ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2017/28

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
http://et.usembassy.gov ይጎብኙ

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) ወላጅ አልባ እና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕጻናትን እየታደገ ነው

አዲስ አበባ፤ መስከረም 19፤2010፡- የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) እና አጋሮቹ ፓክት እና FHI360 እንዲሁም ቻይል ፈንድ፤ በUSAID የሚደገፈው የኮከብ ብርሃን እጅግ ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት መርሀ-ግብር በስኬት መጠናቀቅን እና አዲስ የተጀመረውን በUSAID ድጋፍ በFHI360 የሚተገበረውን እጅግ ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት ክብካቤ መርሐ-ግብርን መጀመር በጋራ አብስረዋል፡፡ እ.አ.አ. ከ2011 ጀምሮ፤ ይህ በአሜሪካ ፕሬዝዳንት የአስቸኳይ ዕቅድ ለኤድስ ድጋፍ (PEPFAR) የሚደገፈው መርሐ-ግብር፤ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመሥራት፤ ወላጅ አልባ እና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕጻናት የኤች አይ ቪ ምርመራ፤ ህክምና እና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች እንዲያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ የመጠለያ፤ የምግብ፤ የትምህርት፤ የህግ እና የስነልቦና ድጋፍ እንዲሁም አቅማቸውን የማጠናከር ሥራ ይሰራል፡፡

92 ሚሊዮን ዶላር ወጪ የተደረገበት የአምስት ዓመት የኮከብ ብርሃን እጅግ ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት መርሐ-ግብር በቅድሚያ በዘጠኝ የሀገሪቱ ክልሎች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ እ.አ.አ. ከ2014 ወዲህ ደግሞ በአማራ፤ ኦሮሚያ፤ ትግራይ፤ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ከ900,000 በላይ የሆኑ ከፍተኛ የኤች አይ ቪ ስርጭት ባለባቸው ከተማ እና ከተማ ቀመስ አካባቢዎች የሚኖሩ እጅግ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕጻናት እና ቤተሰቦቻቸው የመርሐ-ግብሩ ተጠቃሚ ናቸው፡፡

በመርሐ-ግብሩ በተለይ አሰራሮችን በማጠናከር፤ ክብካቤን በማቀናጀት፤ የተሻለ የሪፈራል ግንኙነት በመፍጠር፤ የማኅበረሰብ ኮሚቴዎች እና የተቀናጀ የክብካቤ ሂደትን በማጠናከር፤ የአባወራዎችን የገንዘብ አቅም በማሳደግ፤ እንዲሁም በማስረጃ የተደገፈ የውሳኔ አሰጣጥን በመተግበር ረገድ አመርቂ ውጤት ተገኝቷል፡፡ የሴቶችና ሕጻናት ሚኒስቴር በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የቅድመ-ህጻንነት ዕድገት አገልግሎት ሞዴልን ለማስፋት አቅዷል፡፡

ቀጣዩ የUSAID ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት ክብካቤ መርሐ-ግብር፤ ከኮከብ ብርሃን መርሐ-ግብር ትግበራ የተገኙ ስኬቶችን በመቀመር፤ ወላጅ አልባ እና ለችግር ተጋላጭ ሕጻናትን ጤና እና ደህንነት ለማሻሻል ይሠራል፡፡ ሕጻናት ተኮር እና ቤተሰብን ያማከለ የሁነቶች አስተዳደር የአዲሱ መርሐ-ግብር ዋነኛ የትኩርት መስክ ይሆናል፡፡ መርሐ-ግብሩ ከኅብረተሰቡ በሚውጣጡ ሠራተኞች በመታገዝ፤ ሕጻናትና ቤተሰቦቻቸውን የቤት ለቤት ክትትል በማድረግ፤ እንደ ኤች አይ ቪ/ኤድስ፤ ጤና፤ ስነ-ምግብ፤ የኢኮኖሚ ደህንነት፤ ትምህርት፤ ጥበቃ እና የስነልቦና ድጋፍ አገልግሎቶችን የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

FHI 360 በ22 አገር በቀል አጋር ፈጻሚዎች አማካይነት ከፕላን ኢንተርናሽናል፤ ሪትራክ እና የኢትዮጵያ የሶሺዮሎጂስቶች ማህበር ጋር አጋርነት የፈጠረ ሲሆን፤ ከወሳኝ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በሚሰጠው አመራር ለ325,000 በከፍተኛ ሁኔታ ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት እና ከ170,000 በላይ ክብካቤ ሰጪዎች አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በአማራ፤ ኦሮሚያ፤ ትግራይ፤ እና የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ 126 ወረዳዎች/ከተሞች የሚተገበረው መርሐ-ግብር 49 ሚሊዮን ዶላር ተመድቦለታል፡፡

***

ለተጨማሪ መረጃ https://www.usaid.gov/ethiopia ይጎብኙ